የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ
# HARAR NEGARI GAZETA
## OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

| | | |
|---|---|---|
| 16ኛ ዓመት ቁጥር 7<br>16th Year No. 7 | | ሐረር ሐምሌ 12 ቀን 2003ዓ/ም<br>HARAR, July 13,2011 |
| ያንዱ ዋጋ ብር 3.00<br>Unit Price Birr 3.00 | በሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖ.ሣ.ቁ. 952<br>P.O.Box 952 |


ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 102/2003 ዓ/ም

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የአስፈፃሚ አካላት አደረጃጀት ተጠሪነት ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ .........................ገጽ—784


## አዋጅ ቁጥር 102/2003
## የሀረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት
## የስፖርት ኮሚሽን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በክልሉ ስፖርትን ማስፋፋትና የሕብረተሰቡን በተለይም የወጣቱን ጤንነት በመጠበቅና አእምሮውን በማበልፀግ በሀገርና በክልል ግንባታ ሂደት ንቁ ተሳትፎና ግንኙነቶች ለማዳበር ከፍተኛ አስተዋጽዖ የሚያበረክት በመሆኑ፤

የስፖርት እንቅስቃሴዎችን ለማስፋፋት ለመደገፍና ለመምራት በክልል ደረጃ ራሱን የቻለ ተቋም ማደራጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በተሻሻለው የሀረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ሕገ-መንግስት አንቀጽ 51 (2) (ሀ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ ‹‹ የሀረሪ ህዝብ ክልል መንግስት የስፖርት ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር102/2003 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **መቋቋም**
   1. ከዚህ በኃላ ኮሚሽን እየተባለ የሚጠራ የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ ስፖርት ኮሚሽን በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
   2. ኮሚሽኑ ተጠሪነቱ ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይሆናል፡፡

3. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የኮሚሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት ሀረር ከተማ ነው፡፡

4. **የኮሚሽኑ ዓላማ**

ኮሚሽኑ ዓላማ ሕዝባዊ መሠረት ያለው ስፖርት በክልሉ እንዲስፋፋ ማድረግ እና ምርጥ ስፖርተኞችን ማፍራት ማበረታታት ይሆናል፡፡

5. **የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር**

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

1. ሐገራዊ የስፖርት ፖሊሲዎችን ስትራቴጂዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤
2. በክልሉ ውስጥ ለሚቋቋሙ የስፖርት ማህበራት ፈቃድ ይሰጣል ይሰርዛል፤ ፕሮግራሞችን ያስተባብራል ይቆጣጠራል፤
3. የስፖርት ውድድሮችን እንዲዘጋጁ ያደርጋል ያስተባብራል፣አስፈላጊውን ድጋፍይሰጣል፤
4. በክልሉ የስፖርት ማህበራት መካከል የሚነሱ ክርክሮችን በስፖርት ምክር ቤት እንዲዳኝ ያደርጋል፤
5. በክልሉ የባህል ስፖርት እንዲታወቅና እንዲዘወተር ያደርጋል፤
6. በስፖርት የሠለጠኑ ኃይል ለማፍራት ከሚመለከታቸው አካላት በመተባበር የስፖርት ትጥቆችና መሣሪያዎች አቅርቦት የሚሟላበት ሁኔታ ያመቻቻል፤
7. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የስፖርት ህክምና አገልግሎትያደራጃል፣ በስፖርት አበረታች መድሃኒቶችና ዕፆች መጠቀምን ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤
8. የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ መመሪያ ያወጣል በክልል ደረጃ የሚቋቋሙ የስፖርት ማህበራትን ይመዘግባል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤
9. የንግድ ሥራ ፈቃድን በሚመለከት ለሌሎች አካላት በሕግ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የስፖርት ማህበራት ለዓላማቸው ማስፈፀሚያ የሚውል ገቢ ማመንጨት የሚችሉ ከዓላማቸው ተዛማጅነት ያላቸው ሥራዎች እንዲያከናውኑ ይፈቅዳል፤
10. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል ፣ይከሰሳል፤
11. ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል፤
12. በክልሉ የስፖርት ማዘወተሪያ ሥፍራዎች እንዲዘጋጅ ያደርጋል የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል።

6. **የኮሚሽኑ አቋም**

ኮሚሽኑ፣

1. የክልል የስፖርት ምክር ቤት (ከዚህ በኃላ ምክር ቤት እየተባለ የሚጠራ)፤
2. ኮሚሽኑን የሚመራ ኮሚሽነር በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይሾማል፤
3. አስፈላጊው ሠራተኞች ይኖሩታል።

7. **የምክር ቤቱ አባሎች**

ምክር ቤቱ የሚከተሉት አባሎች ይኖሩታል፤

1. ኮሚሽነሩ..................................ሰብሳቢ
2. ትምህርተ ቢሮ ተወካይ.......................አባል
3. የጤና ጥበቃ ቢሮ ተወካይ.................አባል
4. የክልል ፖሊስ ኮሚሽን ተወካይ..............አባል
5. በክልል አቀፍ ደረጃ የተቋቋመ የስፖርት ማህበራት ተወካዮች.......አባል
6. የባህል ቅርስና ቱሪዝም ቢሮ ተወካይ ........አባል
7. የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት ሥራ አስኪያጅ ተወካይ.............አባል እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች አግባብ ያላቸው በአባልነት ሊያካትት ይችላል።

8. **የምክር ቤቱ ስብሰባ**

1. ምክር ቤቱ በዓመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።
2. ከምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ በስብሰባው ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።
3. የምክር ቤቱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩልበእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው መመሪያ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡

9. **የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር**

ምክር ቤቱ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

1. ስፖርት ስለሚስፋፋበትና ስለሚተዳደርበት ሁኔታ ይመክራል ሃሣብያቀርባል፤

2. ስፖርትን በሚመለከት ለክልሉ መንግስት የሚቀርቡ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ይመክራል ሃሣብ ያቀርባል፤
3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 መሠረት ኮሚሽኑ የሚያወጣቸውን መመሪያዎች ያጸድቃል፡፡

## 10. የኮሚሽነሩ ሥልጣንና ተግባር

1. ኮሚሽነሩ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የኮሚሽኑን ሥራዎችይመራል፤ ያስተዳድራል፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ___ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽነሩ፤
   ሀ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 የተመለከቱትን የኮሚሽኑን ሥልጣንና ተግባሮች ሥራ ላይ ያውላል፤
   ለ. በክልል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት የኮሚሽኑን ሠራተኞች ይቆጣጠራል፣ያስተዳድራል፤
   ሐ. የኮሚሽኑን የሥራ ፕሮግራምና በጀት ያዘጋጃል፣ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤
   መ. ለኮሚሽኑ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ ኮሚሽኑ ይወክላል፤
   ረ. የኮሚሽኑን የሥራ አፈፃፀምና የሂሣብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለመንግስት ያቀርባል፡፡
3. ኮሚሽነሩ ለኮሚሽኑ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኮሚሽኑ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

## 11. በጀት

የኮሚሽኑ በጀት በመንግስት ይመደባል፡፡

## 12. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከሐምሌ 12 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ሙራድ አብዱልሃዲ**

**የሀረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት**

**ፕሬዝዳንት**